# *እውን ኃያሉ አሜሪካ የኢትዮጵያን ጥንካሬ ይፈልጋል ወይ ?*

## *መግቢያ*

ሰሞኑን የቅንጅት መሪዎች ወደ አሜሪካና ወደ አውሮፓ በተለያዩ ከተማዎች በመዘዋወር ስለ ኢትየጵያ ሁኔታና ስለሚቀጥለውም የትግል ስትራቴጂ ለኢትዮጵያውያን ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ስለሰላማዊ ትግልና ስለብሄራዊ እርቅ ጉዳይ ፣ ቅንጅት ወደ ፊት ከኤርትራ ጋር ስለሚኖረው ግኑኝነትና የባድሜን ጉዳይ አስመልክቶ የቦርደር ኮሚሽኑን ውሳኔ የመቀበልና ያለመቀበል ጉዳይ ፣ ቅንጅት በውጪ ኃይሎች ላይ ስለሚኖረው ግኑኝነትና እነዚህም ኃይሎች በምርጫው ውጤት ላይ ስለነበራቸው አቋምና ስለ ብሄራዊ ነፃነት ጥያቄ ጉዳይ ፣ እንዲሁም ቅንጅት በከተማዎች የአስተዳደር ምርጫ ላይ ስለ መካፈሉ ጉዳይ ወዘተ... ወዘተ... ተነስተው ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። እነዚህ ጥያቂዎች የተነሱትና ከልዑካኑ ማብራሪያ የተሰጠው እ.አ. በ 8.10.2007 በበርሊን ከተማ ተገኝተው በአንድ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ለተሰበሰበው ኢትያጵያዊ ነው። ስለዚህም ይህ ዘገባና ሀተታ የበርሊኑን ብቻ ይመለከታል።

በዕለቱ በእነዚህ ጥያቂዎች ላይ ማብራሪያ ለመስጠት የተሞከረ ቢሆንም ፣ ማብራሪያው ከኢትዮጵያ ጥቅም ጋር ይያዝ አይያዝ ፣ መልሶቹ በሙሉ የኢትዮጵያን የወደፊት ዕድል በመወሰን ላይ ስለሚኖራቸው ተፅዕኖና ሚና ፣ እንዲሁም ደግሞ መልሶቹ በሙሉ በእርግጥስ የቅንጅትን አቋም ያንጸባርቁ አያንጸባርቁ ፣ በስበሰባው ላይ የተገኘው ኢትዮጵያዊ የቱን ያህል ይገንዘበው አይገንዘበው ፣ በቅጡ ለማወቅ አይቻልም። በዚህ አጠናቃሪ ታዛቢነት መልስ የተሰጡባቸው ጥያቄዎች በሙሉ አጥጋቢ አይደሉም ብሎ አፉን ሞልቶ ባይናገርም ፣ ጠጋ ብሎ ለመረመራቸው ብዙ እርስ በርሳቸው የሚጋጩና ለወደፊቱም የሀገራችንን ዕድገትና ዕድል ወሳኝ የሆኑ ጥያቄዎች አጥጋቢና ሳይንሳዊ መልስ ተሰጥቶባቸዋል ብሎ በፍጹም አያምንም። ከነዚህ ውስጥ የኤርትራን ነፃነት የማወቁና ያለማወቁ ጉዳይ ፣ የቦርደር ኮሚሽኑን ውሳኔ የመቀበሉና ያለመቀበሉ ጉዳይ በፍጹም አጥጋቢ መልስ አልተሰጠባቸውም። ይህ ጸሀፊ ከፖለቲካ ስሌት አንፃር በማጤን በእነዚህ መሰረታዊ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጥያቄ ላይ አስተያየቱን ከመስጠት ይቆጠባል። በዚህ ጽሁፍ አጠናቃሪ ፣ በተለይም የምርጫውን ውጤት መጨናገፍ ፣ የውጪ ኃይሎች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ህይወት ላይ በአለፉት አስራ አምሰት ዐመታት ስለተጫወቱት ሚና ተለይቶ መታየት ስለሌበት ጉዳይና የዛሬውን አገዛዝ ባህርይ በሚመለከት ስለሰጠው ሰፊ ማብራሪያ ከልዑካኑ አንዱ ከሆኑት የተሰጠው ገለጻ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከታገሉለትና ከሚታገሉለት የብሄራዊ ነፃነት ጥያቄ ጋር በፍጹም ስለማይስማማ ይህንን በዚህች አጭር ዕትም ላይ ያብራራል። የግንቦቱ ምርጫ ሰፊ የህዛባዊ ተሳትፎና ውጤቱም የግዴታ ለብሄራዊ ነፃነትም መከበር የተደረገ ህዝባዊ ወሳኔ በመሆኑ ከልዑካኑ ውስጥ አንዱ ይህንን አስመልክቶ የሰጠው ማብራሪያ የኢትዮጵያን ህዝቦች ጥቅም የሚፃረርና የሀገራችንንም ብሄራዊ ነፃነት የሚቀናቀን መሆኑን ያመለክታል። በመሆኑም አንድ ሀገር ብሄራዊ ነፃነቷን የሚያስከብርላት አገዛዝ ካልተቋቋመ ህዝቡ ህብረተሰብአዊ መተሳሰር ኖሮት የተከበረችና የበለጸገች ሀገር ለመገንባት እንደማይችል ያረጋግጣል። ከዚህም በመነሳት ዕውነተኛ ግለሰብአዊ ነፃነት የግዴታ ከብሄራዊ ነፃነት መከበር ጋር የተያያዘ መሆኑን ፣ ብሄራዊ ነፃነት ካልተከበረ ደግሞ በፍጹም ግለሰብአዊ ነፃነት ሊኖር እንደማይችልና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያንም ለመገንባት እንደማንችል በዚህች አጭር ጽሁፍ ለማሳየት ይሞከራል። በተጨማሪም የአንድ ሀገር ብሄራዊ ነፃነት መከበር የግዴታ ከወስጡ ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ጋር የተያያዘ መሆኑን ፣ይህ በሌለበት ቦታ ደግሞ ስለብሄራዊ ነፃነት መከበርና ስለ ገለሰብአዊ ነፃነት ተግባራዊነት ማውራት እንደማንችል ማረጋገጥ ይቻላል።

## *ግለሰብአዊ ነፃነትና የብሄራዊ ነፃነት መከበር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው !!*

በፍልስፍና ዓለም ውስጥ የተካሄደው ትግል ወደድንም ጠላንም ግለሰቦች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚናና እያንዳንዱም ግለሰብ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ

የማሰብ ችሎታውን ተጠቅሞ የሚፈለግውን ነገር እንዴት ተግባራዊ ለማድረግ ይችላል የሚል ነው። ስለሆነም በፍልስፍናዊ ላይ በተመሰረተ ዕውቀት መሰረት ልዩ ልዩ ተፈጥሮአዊ ነገሮች የሚንቀሳቀሱበትና የሚያድጉበት የራሳቸው የሆኑ ውስጣዊ ህጎች አሏቸው። ይሁንና በደንብ ሊዳብሩና ውጤት ሊሰጡ የሚችሉት ደግሞ በአከባቢያቸው ያሉ ሌሎች ነገሮች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው። አትክልቶችና ዛፎች ለማደግ የሚያስችላቸው ውስጣዊ የተፈጥሮ ህግ ሲኖራቸው ፣ ሊስፋፉና ሊያብቡ የሚችሉት ደግሞ ከነሱ ቁጥጥር ውጭ ያሉ እንደ ፀሀይና ዝናብ እንዲሁም ደግሞ ልዩ ልዩ ንጥረ-ነገሮች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው። በሌላ አነጋገር በነጠላ ነገሮችና በአካባቢው በሚገኙ ልዩ ልዩ ነገሮች መሀከል መፈላለግና ጥገኝነት አለ። በሌላ ወገን ከነጠላ ነገሮች ውጪ የሚገኙ ለምሳሌ እንደ ፀሀይ የመሳሰሉ ነገሮች ሙቀታቸው ተፈጥሮአዊ ነገሮች ከሚፈልጓቸው በላይ ከሆነና የሙቀቱም መጠን ከፍ እያለ ከሄደ ከጠቃሚነቱ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ይህ እንዳይሆን ግን ተፈጥሮ ረሷን የምትቆጣጠርባቸው ውስጣዊ ህጎች አሏት። በሌላ በኩል ግን የሰው ልጅ አርቆ ባለማሰብ የሚወስዳቸው አካባቢን የሚጎዱ ነገሮች የግዴታ የተፈጥሮን ውስጣዊ ህግጋት ይጎዳሉ። መዛባትን ያስከትላሉ። በመሆኑም በሰው ልጅና በተፈጥሮ መሀከል ያለው ግኑኝነት ሲዛባ የሰው ልጅም ጤንነት ይቃወሳል። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሄርም ይሁን ሌላ ነገር ተፈጥሮን አስተካክሎልን ፈጥሯል ማለት ይቻላል። ይህ ውስጣዊ የቁጥጥር ህግ( self regulating mechanism) ባይኖር ኑሮ ተፈጥሮ ትዛባለች። የሰው ልጅም በዚህች ምድር ሊኖር ባልቻለ ነበር። ለዚህ ነው ላይብኒዝ እግዚአብሄር ከሌሎች ፕላኔቶች ይልቅ ቆንጆዋንና ሁሉን ነገር አሟልቶ የፈጠረልንን ምድርን ከሁሉም የበለጠች ፕላኔት ብሎ የሚጠራት።

የጥንት ፈላስፎች በግለሰብ ነፃነት ላይ ያተኮሩት የሰው ልጅ በአፈጣጠሩ አርቆ የሚያስብ ውስጣዊ አካል(rational being) እንዳለው ፣ ይሁንና ግን ይህ ክፍል በተለያዩ ሁኔታዎች እንደሚሸፈንና በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ ማየት የሚችላቸውን ነገሮች ማየት የማይችልበት ሁኔታ እንደሚፈጠርና የሚያየውን ችግር ከመፍታት ይልቅ የሚያባብስ ወይም ሌላ ችግር የሚፈጥርና ነፃነትን ከመቀዳጀት ይልቅ በጨለማ ዓለም ውስጥ መኖር እንደ ሚገደድ ነው። አንድ ህዝብ ወይም ግለሰብ አርቆ የማሰብ ኃይሉን ለመጠቀም የማይችለው አይ በተሰሳተ ርዕዮተ-ዓለምና ባህል ስለሚጠመድ ወይም ደግሞ የተወሰነ አገዛዝ በሚፈጥረው ጭቆናና በሚፈጥረው ስርዓት ካለበት ሁኔታ አርቆ ማሰብ እንዳይችል በሚደረግበት ጊዜ ነው። የሚኖርበት ሁኔታ መጥፎ ቢሆንም ያንን እንደ ተፈጥሮአዊ በመውሰድ በዚያ መንፈሱንና የማቴሪያል ሁኔታውን በሚያዳክመው የኑሮ ሁኔታ እንዲገፋበት ይገደዳል። ከዚህ የማሰብ ኃይልን ከሚያዳክም ፣ ከብርሀን ይልቅ ጨለማን ከሚያሰፍን ኑሮ እንዲላቀቅ ለማድረግ ማንኛውም ግለሰብ ነፃ መሆኑንና የመፍጠር ኃይል እንዳለው መረዳት አለበት።ስለዚህም ዕውነትን ከዕውሸት ሊለይ የሚችልበት የፍልስፍና መሳሪያ ያስፈልገዋል። ይህ ሲሆን ብቻ ማንኛውም ግለሰብ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ሚና መረዳት ይችላል። ታሪክን የሚሰራ መሆኑን ይገነዘባል። ከጥፋት ይልቅ ወደ ጥሩ ነገር መስራት በማምራት ፣ ከራስ ጥቅም ባሻገር ስራውን ከሌሎች እሱን ከመሰሉት ጋር በማቀናጀት ህብረተሰብአዊ ኃይል በመሆን የስልጣኔ ባለቤት ይሆናል። ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ነፃነቱንና የመፍጠር ኃይሉን ማዳበር የሚችለው በተወሰነ ህብረተሰብ ውስጥ ብቻ ነው። ግለሰብአዊ ነፃነትና ህብረተሰብአዊ ነፃነት አንድ ላይ ተያይዘው የሚሄዱ እንጂ በፍጹም ሆድና ጀርባ ሆነው የሚተያዩ አይደሉም።

ፕላቶንና በሱ እግር የተተኩ ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች በነጠላ ነገሮችና በዩኒቨርስ መሀከል መተሳሰር እንዳለ ፣ ነጠላ ነገሮች ደግሞ የየራሳቸውም ውስጣዊ ህጎች ቢኖራቸውም በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ብቻ መዳብራና መፋፋት እንደሚችሉ ይናገራሉ። ለዚህም ነው የሰው ልጅ እንደ ሌሎች ፍጡር ነገሮች ሁሉ የራሱ የሆኑ ውስጣዊ ህግና እንዲሁም የማቴሪያልና የመንፈስ ፍላጎት እንዳሉት ፣ እነዚህም ነገሮች ሲሟሉ ብቻ ራሱን ማወቅ እንደሚችልና በሱና በሌሎች የህብረተሰብ አካሎች መሀከል የግዴታ መተሳሰሮች እንዳሉ ፣ ማንም ግለሰብ ብቻውን ቢከንፍና የራሴን ጥቅም ብቻ አሳድዳለሁ ቢል የትም ሊደርስ እንደማይችል ያስተማሩት። በዚህም መሰረት ግለሰቦች ሲተሳሰሩና ወደ ማህበረሰብ ሲያመሩና ወደ ሀገር መመስረት ሲሸጋገሩ የግዴታ ራሳቸውን ከዚያ ከተወለዱበትና ካደጉበት ማህበረሰብና ሀገር ጋር ማገናኘትና ሀገሬ ነው ብለው መጥራት የጀመሩት። የሀገር መመስረት ጉዳይና ራስን ከመጡበት ሀገር ጋር የማገናኘቱ ጉዳይና እንዲሁም ደግሞ በዚያ ሀገሬ ተብሎ በሚጠራው ህብረተሰብ ውስጥ ራስን መቻልና መዳበር እንዲሁም ደግሞ ታሪካዊ ግዴታን መወጣት በተለያዩ ምክንያቶች በተለያዩ ሀገሮች ልዩ ልዩ መልክ ይዞ ዛሬ እያንዳንዱ ሀገር እንደ ሀገር ታውቆ የራሱ ባንዲራ ኑሮት ፣ ግለሰቦችም የዚህ ወይም የዚያኛው ሀገር ዜጋ ተብለው እንዲታወቁ ሆነዋል።

በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ፣ በተለይም ፍልስፍናና ሳይንስ ዳብረው ህብረተሰቦች እየተረጋጉ ሲመጡ የግዴታ የግለሰቦች ሚናና፣ በአንድ በኩል በግለሰቦችና በጠቅላላው ህብረተሰብ መሀከል የሚኖረው ግኑኝነት፣ በሌላ ወገን ደግሞ በህብረተሰብና በሀገር መሀከል ያለው ግኑኝነት ልዩ ልዩ ትርጉም ተሰጥቶታል። የሀገር ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ፣ የነሆበስ፣ ጆን ሎክና አዳም ስሚዝ ፍልስፍናና የኢኮኖሚ ዕውቀት እየተስፋፉ ሲመጣ ግለ ሰቦች የህብረተሰብ አካል መሆናቸው ቀርቶ የየራሳቸውን ጥቅም አሳዳጅ ሆነው መታየትና ሊዚህም በውስጣዊ የግለሰብ ፍላጎትና ጥቅምን አሳዳጅነት እንደሚገዙና እንደሚተዳደሩ ተቀባይነት እንዲኖረው መሰበክ ተጀመረ። ይሁንና ይህ ዐይነቱ ፍልስፍና እያየለ ቢመጣም የተወሰኑ አውሮፓ ሀገሮች አገዛዝ ንቃተ ህሊና የግዴታ ሀገርና ህብረተሰብ መያያዝ እንዳለባቸው፣ ስለዚህም እያንዳንዱ ሀገር ነፃ ነው የሚለው መሰረታዊ አስተሳሰብ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደረገ። በተለይም ከሰላሳ ዐመቱ የካቶሊኮችና የፕሮቴስታንቶች ጦርነት በኋላ በዌስት ፋሊያ ስምምነት መሰረት እ.አ በ1648 ዓ.ም የተደረሰበት ድምደማ እያንዳንዱ የአውሮፓ ሀገር ነፃ መንግስት (sovereign state) ነው የሚልና ማንኛው ሀገር በሌላው ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ነው። በዚህም መሰረት በጊዜው ስልጣን የያዙት የንጉሰ ነገስታት አገዛዞች በዚህ ብቻ እንደማይረኩና የግዴታ ወደ ውስጥ ህብረተሰቡን ለማስተሳሰርና እያንዳንዱ ዜጋ ሀገሬ ነው ብሎ እንዲገነዘብ ወደ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ማምጣት እንደተገነዘቡና ለዚህም የግዴታ የማኑፋክቱር አብዮት ማካሄድ እንዳለባቸው ተረድተው ቆርጠው የተነሱት። እነዚህ ውስጣዊ መስተካከያዎችና ማሻሻያ እርምጃዎች ደግሞ ከእንግሊዝ በሚመጣ የነፃ ንግድ ፍልስፍና ግፊት እንደተደረገባቸውና አንዳንድ ሀገሮችም በጀመሩት የኢንዱስትሪ አብዮት እንዳይገፉበት ማዕቀብ ይደረግባቸው ነበር። ይህንን የተረዱት በጊዜው የተነሱት የየሀገሩ ምሁሮች የእንግሊዝን ተንኮል መቋቋም እንዳለባቸውና የግዴታ በማኑፋክቱር አብዮት አማካይነት ብቻ ነፃ ሀገር የሚለው መሰረታዊ ሃሳብ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችልና ግለሰብአዊ ነፃነትም እንደሚገኝ ማስተማር የጀመሩት። የመርካንታሊስቶች የኢኮኖሚ ፍልስፍናና በዚህ ላይ የተመሰረተው የእነ ፍሪድርሽ ሊስት ብሄራዊ የኢኮኖሚ ትምህርት ለዚህ የእነ አዳም ስሚዝ የነፃ ንግድና የዓለም አቀፍ የስራ ክፍፍል መልስ ሆነው ለመውጣትና ጀርመንን በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢንዱስትርና በዕደ ጥበብ እንድታድግ ለማድረግ የበቁት። በዚህ የጀርመን ኢኮኖሚ ዕድገትና በአጭር ጊዜ ውስጥ እንግሊዝን መስተካከል የተለያዩ ፈላስፋዎችና ገጣሚዎች አስተዋፅዖ እንዳለበት ግልጽ ነው። በነዚህ ፈላስፎች ዕምነት አንድ ሀገር እንደ ህብረተሰብ መቆጠር የምትችለውና እንደ ነፃ ሀገር የምትታወቀውና የምትከበረው በሁሉም መስክ የዳበረች እንደሆን ብቻ ነው። በመሆኑም ልዩ ልዩ ጥበባዊ ነገሮች፣ እንደ ጥንታዊ የህንፃ አሰራርና(classical architecture) መናፈሻ ቦታዎች፣ ቲያትርና ሙዚቃ እንዲሁም ስዕል፣ እነዚህን የመሳሰሉት ለአንድ ህብረ-ብሄር መመስረትና ለብሄራዊ ነፃነት መከበር ቅድመ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ አንድ ህዝብ የመፍጠር ኃይሉ ሊዳብር የሚችለውና ማንነቱን የሚያውቀው እነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ሲሟሉ ብቻ ነው። እነዚህ መሰረታዊ የኪነት ነገሮች ባልተሟሉበት ቦታ አንድ ህብረተሰብ ወይም ግለሰቦች እንደ ነፃ ህዝብ መኖር አይችሉም። ለዚህም ደግሞ የግዴታ የትምህርት መስኩ መሰረታዊ ለውጥ መደረግ አለበት። የግለሰቦችን ጭንቅላት የሚያድስ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ በራሱ ላይ ዕምነት እንዲኖረውና የመፍጠር ችሎታውም ከፍ እንዲል በግሪክ ክላሲኮች ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ የትምህርት ስርዓት መነደፍና ተግባራዊ መሆን ነበረበት። ለትምህርት ዘርፉ መሰረታዊ ለውጥ ሁምቦልድት የተባለው ታላቅ ፈላስፋ አስተዋፅዖ አድርጓል። በእነዚህ አዋቂዎች ዕምነት ችግር፣ ረሀብና ጦርነት አርቆ ከማሰብ ጉድለት የሚከሰቱ ህብረተሰብአዊ ክስተቶች ናቸው። እንደዚሁም አንድ ህብረተሰብ ሰፋ ያለና ጠለቅ ያለ ዕውቀት ከሌለው በቀላሉም ለጦርነት ባሰፈሰፉና ጦርነት ሙያቸው በሆኑ ሰዎች እየታለለ የጦርነት እራት ይሆናል። ወረራና ጦርነትም ከጭንቅላት ውዝግብ የሚፈጠሩ በተለይም ኢምፔሪያል ፍላጎት ባላቸው ኃይሎች የሚቆሰቆስ ነው። በታሪክ እንደታየውም፣ ግሪክ ማበጥ ስትጀምር በስፓርታ ላይ ዘመቻ ከፈተች። የሮማውያን አገዛዝና ውድቀት፣ በተለያዩ ጊዜ ሀይማኖትን ተገን አድርገው የተነሱ ጦርነቶች በቀጥታ ኢምፔሪያላዊ ከሆነ የሌላውን ህብረተሰብ ውስጣዊ ሂደት ለመቅጨት የተካሄዱ ጦርነቶች ናቸው። የአንደኛውና የሁለተኛው ዓለም ጦርነቶች፣ ባለፉት ስድሳ ዐመታት በተለይም በአፍሪቃና በላቲን አሜሪካ የሚካሄዱት ትናንሽ ጦርነቶች በመባል የሚታወቁት ድብቅ ጦርነቶች፣ ዛሬም በአፍሪቃ ቀንድ የሚካሄደው ህዝባችንን የሚያሰቃየው ጦርነት በተዘዋዋሪ የህብረ-ብሄርን መገንባትና መጠንከር በሚፈታተኑ ኢምፔሪያል ኃይሎች የሚቆሰቆስ የውክልና ጦርነት (proxy war) ነው። በሌላ አነጋገር አውሮፓና አሜሪካ የሚሰሩትን የጦር መሳሪያዎች ጦርነትን ወደኛ በማምጣት መፈተሽ አለባቸው። በአንፃሩ ግን እነሱ እንደ ህብረ-ብሄር ጠንክረው የሌላውን ዓለም ህዝብ የመኖርና ያለመኖር ዕድል በመወሰን ውስጣዊ ሂደት እንዲዛባና የህዝቦች አትኩሮ በጦርነት ላይ ብቻ እንዲሆን ያደርጋሉ።

ወደ ሀገራችንና ወደ ብዙ አፍሪቃ አገሮች ስንመጣ በባሪያ ንግድ ፣ በቅኝ ግዛትና የኋላ ኋላ ደግሞ በተጫነብን ዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍልና ንግድ አማካይነት ህብረተሰብን የመመስረትና ሀገርን እንደ ነፃ ሀገር የመገንባቱ ጉዳይ ተፈጥሮአዊ ጉዞውን ይዞ ሊሄድ አልቻለም። በተለይም ብዙ የአፍሪቃ ሀገሮች የባሪያ ንግድና የቅኝ ግዛት አስተዳደር ባደረሰባቸው ጉዳት ከወደቁበት ለመነሳት በፍጹም አልቻሉም። የፖለቲካን ነፃነት ከተቀዳጁም በኋላም በየጊዜው በሚካሄድባቸው የመንግስት ግልበጣና የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ግብነትና ወደ ጦርነት ዓለም ውስጥ መዝፈቅ ህብረተሰቦቻቸውን እንደ ህብረተሰብና ሀገሮቻቸውን እንደ ነፃ ሀገር መመስረትና ማጠንከር በፍጹም አልቻሉም። የርዕዮተ ዓለም ውዥንብራና የባህል ተፅዕኖ ተጨምሮበት ዛሬ ብዙ የአፍርቃ ሀገሮች አቅጣጫቸውን እንዲስቱና እንደ ህብረተሰብ ለመኖርና ለመዳበር እንዳይችሉ ተደርገዋል። በተለያዩ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በመመራትና ተግባራዊ በማድረግ ባለፉት ስድሳ ዓመታት የደረሰባቸው ግፊትና ድቀት አሁን በዘመነ ግሎባላይዜሽን እየተጠናከረ መጥቶ እዚያው በዚያው እንዲታሹና ዜጎቻቸውም እንዲሰደዱ በቅተዋል። ግሎባላይዜሽንና የነፃ ንግድ እንደ ማስፈራሪያ ሆነው በመቅረብ ፣ ይህንን ያልተቀበለ ፣ እዚህኛው ወይም እዚያኛው ዓለም አቀፋዊ የንግድ ድርጅት ውስጥና ልዩ ልዩ ኢኮኖሚ መዋቅሮች ውስጥ መግባት አይችልም ፣ ዕርዳታም አያገኝም ፣ ዕቃውንም በቀላሉ በዓለም ገበያ ላይ ሊሸጥ አይችልም እየተባለ ማስፈራሪያ ስለሚደርስበት በተለይም ብዙ የአፍሪቃ ሀገሮች መዋከብ ደርሶባቸዋል። ህዝቦቻቸውን ማስተዳደር የማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል። ሀብቶቻቸው እየተዘረፈና ከፍተኛ የአካባቢ መቃወስና የጤንነት ጉዳት እየደረሰ ይገኛሉ።የምዕራቡ ዓለም ቅጥ ያጣ የበላይነትና ዘረፋ ፣ እንደዚህም ደግሞ ጥቂት የየሀገሮችን ኤሊቶች ተገን አድርጎ በመንግስት መኪና ውስጥ መግባት ብዙ የአፍሪቃ ሀገሮችን ራሳቸውን እንዳይችሉና ነፃ መንግስት እንዳይገነቡ አግዷቸዋል። ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በአንድ በኩል ውስጣዊ ሁኔታና ተፈጥሮአዊ የማደግ ኃይል እንዲበላሽና እዚያው ቀጭጮ እንዲቀር መደረግ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የወጪው ግፊት ከፍተኛ መሆን ብዙ የአፍሪቃ ሀገሮችን አላላውስ ብሏል። ብዙ የአፍሪቃ ሀገሮች ህብረተሰብን ሚዛናዊ በሆነ መልክ መገንባትና ውስጣዊ ሰላምን አስፍኖ ከውጪ የሚመጣን ግፊትም ሆነ ወረራ ለመቋቋም የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

## <u>የኢትዮጵያ ጉዳይ</u>

ብዙ ጊዜ ስለ ሀገራችን ሲወራ ታሪክና ሳይንስ ይምታታሉ። በሌላ ወገን ደግሞ በሁለቱ መሀከል ውስጣዊ ግኑኝነትና ተወራራሽነት እንዳሉ ግልጽ ነው። ይሁንና ታሪክ ከህብረተስብ ክንውን ፣ ከዕድገትና እንደ ሀገር ጠንክሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከብሮ መኖር ተነጥሎ ሲታይ ሳይንስነቱን ያጣል። ታሪክ ሳይንስ መሆኑ ቀርቶ ተረት ተረት ይሆናል።

ኢትዮጵያ ከሶስት ሺህ ዐመት በላይ የሚጠጋ ታሪክ እንዳላት የተረጋገጠ ነው። በዚህ የረዥም ታሪኳ ለስልጣኔና ለዕድገት የሚያመቹ ሁኔታዎች እዚህና እዚያ መመስረት እንደቻሉ ግልጽ ነው። እነዚህ እዚህና እዚያ ካለምንም ውስጣዊ ግኑኝነት ተሰበጣጥረው ይገኙ የነበሩ የስልጣኔ መሰረቶች አንድም በራሳቸው የውስጣዊ ድክመት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በየጊዜው በተነሱት አገዛዝ ድክመትና በቂ የምሁር እንቅስቃሴ ታሪክ አለመኖር ምክንያት የተነሳ ወደ ህብረተሰብአዊ መተሳሰርና ወደ ሀገር ጥንካሬነት ለማምራት አልተቻለም። እዚህና እዚያ የተሰበጣጠረውን ኃይልና የስራ ክፍፍል ሊያስተሳስርና ሊመራ የሚችል ኃይል ብቅ ለማለት ባለመቻሉ የኢትዮጵያ ህዝቦች ኑሮ እንዲቀጭጭ ተገደደ። የዕደ ጥበብ ዘርፉ ደካማ መሰረት ፣ ህብረተሰብአዊ ተቀባይነት ለማግኘት አለመቻል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የሰውን ተፈጥሮአዊ የማቴሪያል ፍላጎት እንዲታፈን ማድረግና አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በተወሰኑና ተደጋጋሚ የፍጆታ ዕቃዎች ብቻ እንዲረካ መደረግ ፣ የኑሮን ትርጉም በዚያው ክልል ብቻ ማሰብና ሌላ አማራጭ እንዳለ አለመረዳት ፣ በዕደ ጥበብ ዘርፍና በሌሎች የምርት መስኮች መሀከል ግኑኝነት አለመኖር ህብረተሰብአዊ መተሳሰር እንዳይኖር አግዷል። ስለሆነም ግለሰብአዊ ምኞትና የፈጠራ ችሎታ ሊዳብሩና ህብረተሰቡም ነፃነት ሊሰማውና ነፃነት እንደሚያሰፈልገው ግንዛቤ ውስጥ አልገባም። ይሁንና ይህ ውስጣዊ ድክመት እያለ ከየቦታው ባህርን ተሻግረው ሀገራችንን ለመውረርና ለመቆጣጠር የመጡ ኃይሎችን ተቋቁመው በጋራ መልሰዋል። በተለያየ ጊዜ የተነሱ ከዚህም ሆነ ከዚያኛው ብሄረ-ሰብ የመጡ ነገስታት ሀገራቸውን ለውጪ ወራሪ ኃይል አሳልፈው ላለመስጠት ቆርጠው በመነሳት ታሪክ የጣለባቸውን አደራ ተወጥተዋል። በኋላም የቴክኖሎጂን ምንነት በመረዳት ፣ የዚህ መሰረቱ እስካልተጣለ ድረስ ሀገራችን ለመጠንከርና እንደ ህብረተሰብ ለመኖር እንደማትችል በመገንዘብ የተለያዩ ነገስታት ቴክኖሎጂ ከውጪ እንዲመጣ

ከአውሮፓ ነገስታት ጋር ይጻጻፉ እንደነበርና ለጥያቂያቸውም አጥጋቢ መልስ እንዳለገኙ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። የህብረ-ብሄር ጥንስሱ በአፄ ዮሃንስና በአፄ ቴዎድሮስ የተጣለ ቢሆንም ፣ መልክ እየያዘ የመጣው በአፄ ምኒልክ አገዛዝ አማካይነት እንደነበር ይታወቃል።

ይህንን የኢትዮጵያን ነገስታት ጠንካራ ሀገር የመመስረት ፍላጎት የተገነዘቡት የአውሮፓ መንግስታት ፣ በተለይም እንግሊዝ ሂደቱ እንዲጨናገፍ ያላደረገችው ጥረት ይህ ነው አይባልም። እንደሌሎች የቅኝ ግዛቶቿ ለመያዝ ባለመቻሏ ጣልያን ኢትየጵያን ቅኝ ግዛት እንድታደርጋት መንገዱን አመቻችታ አሳልፋ ሰጥታለች። በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ የህብረ-ብሄሮችን አገነባብ ጠንቅቃ የምታውቀው እንግሊዝ በአፍሪቃ ምድር ውስጥ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላትን ኢትዮጵያን የመሰለች ሀገር ህብረ-ብሄርን የመመስረት ዕድል በምንም ምክንያት ማግኘት የለባትም በሚለው የተደበቀ አላማዋ ከውጪ በመጣ ጭንቀት ተወጥራ እንድትኖር አድርጋለች። በተለይም በሁለተኛው የኢትዮጵያና የኢጣሊያን ጦርነት ወቅት የኢትዮጵያ ጀግኖች በዱርና በገደል ሲዋደቁ ዕርዳታ በሚያሰፈልጋቸው ወቅት ስታደባ እንደ ነበር ይታወቃል። ኋላ የኢትዮጵያ ጀግኖች ቀስ በቀስ እያሉ በእርግጥም ደግሞ ጠላትን እያጠቁ ሲመጡና ድል በድልም ሲጎናጸፉ ስታይ ይህንን የጀግኖች ድል እንደ አጋዥ ሰርጋ በመግባት ዕውነተኛውን የብሄራዊ-ነፃነት ድል ለማጨናገፍ በቅታለች። አፄ ኃይለ ስላሴ በድል አድራጊነት ወደ ሀገር ከተመለሱ በኋላ ደግሞ በአንድ በኩል ውስጣዊ መርዟን መነስነስ ጀመረች ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ጣሊያን የተከለችውን ኢንዱስትሪና ሌሎች የመገናኛ መሳሪያዎች እየነቃቀለችና አዎሮፐላኖችንም እየለቃቀመች ወሰደች። ጠላት የኢትዮጵያን ህዝብ በመርዝ ጪስ እየደበደበ የተከለውን ንብረትና ኢንዱስትሪ ኋላ ሀገሩን ሊገነባ እንዳይችል ጠራርጋ የወሰደችው ይህንን የኢትዮጵያን ህዝቦችና ጀግኖች እንደ ሀገር ጠንክሮ መውጣት ፍላጎት ጠንቅቃ በማወቋ ነው። ከዚህም አልፋ ለራሷ በሚስማማ መልክ ብቻ በተወሰኑ ቦታዎች ቢሮክራሲያዊ መዋቅሮች ስትዘረጋ ይህም እንዳይስፋፋ ማዕቀቦች በማድረግ ነው። በሷ አምሳል የፈጠረችው ቢሮክራሲና በኋላ በአሜሪካኖች እየተጠናከረ የመጣው በምንም ዐይነት ውስጣዊ ኃይል ኑሮት ወደ ውስጥ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰብአዊ ዕድገትን እንዳያመጣ ታስቦ ነው። በዚህም ምክንያት አንድ ሀገር በሁለት አስተዳደራዊ መዋቅር ስር እንዲወድቅ ተገደደ። ዘመናዊና ኋላ ቀር የሆኑ የአስተዳደር መዋቅሮች እዚያው በዚያው እየተጋፉ ለዕድገት እንቅፋት ሆኑ።

ኢትዮጵያ ይበልጥ በዓለም ገበያ ስር ስትገባና ለውጪ ምንዛሪ በተወሰኑ ጥሬ ሀብቶች ላይ ብቻ እንድትመካ ስትገደድ ፣ ወደ ውስጥ ደግሞ በገጠርና በከተማ መሀከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መጣ። በከተማ ውስጥ ያለውም ልዩነት ዝብርቅር ከመሆኑም በላይ መልክ ላለው ዕድገት እንቅፋት ሆነ። በህብረተሰቡ መሀከል ያለው ልዩነት እየጎላ መጣ። በእንግሊዝ ፣ በኋላ ደግሞ በአሜሪካን የተገነባው አገዛዙና ቢሮክራሲው ለራሳቸው እየጠነከሩና ከህዝቡ እየራቁ በመምጣት ለህብረተሰብአዊና ለኢኮኖሚ ዕድገት እንቅፋት ሆኑ።ይህንን ያመቻቸው አሜሪካ በተለይም በሲቪልና በሚሊታሪ ቢሮክራሲ ውስጥ በመግባትና የስለላውን መረብ በመዘርጋት መንግስቱ ህብረተሰብአዊ ኃላፊነቱን እንዳይወጣ አገደው። ከሁለት ጋሻ በሚበልጥ መሬት ላይ ኤምባሲውን እንዲሰራ የተሰጠውን ዕድል በመጠቀምና የቃኘውን የጦር ሰፈር ተገን በማድረግ ኢትዮጵያ ከውስጥ እንድትቦረቦርና እንደ ህብረ-ብሄርና እንደ ህብረተሰብ እንዳትገነባና እንዳትጠነክር ተንኮሉን መሸረብ ተያያዘው። ይህ ጉዳይ በተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ላይ የመሸነፍን ፣ የመታለልንና የመገዛትን ሁኔታ ፈጠረ። በቀላሉ የሚታለልና ልቡን ከፍቶ የሚሰጥ ኃይል በቅ በማለት ታማኝነቱን ለሀገሩና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ከማድረግ ይልቅ ለአማሪካኖች ማድረግ ጀመረ። በዚያው መጠንም የህብረተሰቡ ባህል ዝብርቅርቅነትና ከሳይንስ ውጭ መሆን የህዝቡን መንፈስ አላላው። በዚህ መልክ የተቦረቦረው የኢትዮጵያ ህብረተሰብና አገዛዙ ከውስጥም ሆነ ከውጪ በሚመጣ ግፊት በመወጠር እንደ ሀገር መንቀሳቀስ የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። አገዛዙ መፍረክረክ ጀመረ። ዕጣው በታሪክ መታለፍ እንጂ በምንም ዐይነት በአዲስ መንፈስና ፍልስፍና ተደራጅቶ የኢትዮጵያን ህዝቦች ዕድል በፍጹም ሊወስን አልቻለም። የአፄው አገዛዝ እስከወደቀ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ህብረተሰቡን የሚያስተሳስርና እንደ አንድ ኃይል የሚያደርገው ፍልስፍና አልነበረውም። የትምህርት መስኩም ለዚህ የተደራጀ ባላመሆኑ ተማርኩ በሚለውና በሰፊው ህዝብ መሀከል ግልጽ ልዩነትና ውስጣዊ መቃቃር ተፈጠረ። በአንድ በኩል ተማርኩ የሚለው አዲስ ኃይል የድሮውን የሚንቅ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ዘመናዊ የሚለውን ትምህርት በደንብ ከራሱ ጋር ያላዋሀደ ነበር። ጉዞው ወዴት እንደሆነ ማወቅ ግራ የገባው የህብረተሰብ ክፍል ብቅ አለ። ይህን ችግር ይህ አዲስ ኃይል የፈጠረው ሳይሆን የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የተዛባ አወቃቀር ውጤት ሲሆን ፣ የአገዛዙንም ዝቅ ያለ የታሪክ ንቃት ህሊና ያንፀባርቃል። ይህንን ሁኔታ ከጃፓኑ የሜጂ ዴናስቲ የጥገና ይሁን ደግሞ መሰረታዊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ እንዲሁም ቀስ በቀስ የህብረተሰብ ለውጥ ጋር ማወዳደር ይቻላል።

የአገዛዙ መውደቅና በታሪክ መታለፍ በሳይንስና በሳይንስ ላይ በተመሰረተ ባህል ለመደራጀት ባለመቻሉ ብቻ ነው። አዳዲስ ህብረተሰብአዊና ዓለም አቀፋዊ ቀውሶች ሲከሰቱ እነዚህን ለመቋቋም የሚያስችለው መሳሪያ የሌለው ህብረተሰብአችን ዕጣው ለረሀብ ፣ ለድህነትና ለጦርነት መጋፌጥ ሆነ። ከሰላሳ ዐመት በላይ የፈጀው የርስ በርስ ጦርነት ከዚህ ባህላዊ ዝብርቅርቀነትና የሀገርንን ምንነት ካለመረዳትም የተነሳ የማያስፈልግ ጦርነት የመነጨ ነው። በተጨማሪም ይህ ዐይነቱ ህብረተሰብአዊ ዝብርቅርቅነትና የኢኮኖሚያዊ ዕድገት መዛባት እዚህና እዚያ ነፃ እወጣለሁ ብሎ ለተነሳው የብሄረ-ሰብ ኃይል አመቺ ሁኔታን እየፈጠረለትና ብሄራዊ ባህርዩም እየተሟጠጠ እንዲመጣ ያደረገና የበለጠ በውጪ ኃይሎች መዳፍ ስር እንዲወድቅና የሀገራችንን ህልውና እንዲፈታተን ያደረገ ነው። በሌላ አነጋገር ከውጪ የመጣው የተዘበራረቀ ባህልና ሳይንሳዊ መሰረት የሌለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፣ እንዲሁም ደግሞ አገዛዙ በአሜሪካን ጉያ ስር እየወደቀ መምጣት ብሄረተኛ የሆነ ኃይልና ሀገር ወዳድ ብቅ እንዳይል አገደው። አሜሪካን ሳይጠብቀው የየካቲቱ አብዮት ሲፈነዳ ፣ ይህ ሁኔታ የበለጠ ወደ መመሰቃቀል ማምራት ነበረበት። የርስ በርስ ጦርነት መከፈት ነበረበት። ለዚህም ደግሞ አሜሪካ በዚህም በዚያም ብሎ የራሱን ሰዎች እየመለመለ የሚሊታሪው ቢሮክራሲ ውስጥ ማስገባት ነበረበት። ሀገራችንን ወደ ጦር አውድማ በመለወጥ የጠነከረ ህብረ-ብሄርና ህብረተሰብ የመገንባቱ ነገር ለብዙ መቶ ዐመታት መሸጋገር አለበት። ልክ በብዙ ላቲን አሜሪካ ሀገሮች እንደታየው ገሚሱ ኮሙኒስት እየተባለ እየተፈረጀበት ሌላው ደግሞ የአሜሪካን ወዳጅ እየተበላ እተወደሰና እየተጃጃለ ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ኃይሎች ወደ ርስ በርስ ጦርነት አመሩ። በመጀመሪያ ጦርነቱ ለአንድ ርዕዮተ ዓለም እንታገላለን ብለው በተነሱ ኃይሎች መሀከል የተፈጠረ ቢሆንም ፣ በአሜሪካን ፍቅር ያበደው ተንኮለኛው የሲቪልና የሚሊታሪ ቢሮክራሲ ሁኔታው እንዲጧጧፍ ያላደረገው ጥረት ይህ ነው አይባልም። በአብዮቱ እንቅስቃሴ ውስጥ በመግባትና እራሱን በመለወጥ ከውስጥ ሆኖ ሁኔታዎችንም ማበላሸት ነበረበት። ይህ ደግሞ የሚገርም ነገር አይደለም። በሳይንስ ላይ የተመሰረተ ከበርቴያዊ ባህል ባላደገበትና ሳይንስና ቴክኖሎጂ የኢኮኖሚው ዕድገት መሰረቶች መሆናቸው በማይታወቅበት ሀገር ብሄራዊ ባህርይና ሀገር ወዳድነት በፍጹም ሊያድጉና ሊያብቡ አይችሉም። ስርም ሊሰዱም አይችሉም። ብሄረተኛ ኃይል እንዲወጣና ሀገሩን እንዲያስከብር ከተፈለገ ደግሞ የግዴታ በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ሰፋ ያለ የባህል ለውጥ መካሄድ ያስፈልጋል። የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል የማሰብና አርቆ የማስተዋል ኃይሉ መዳበር አለበት። በሀገራችን ምድር እንደዚህ ዐይነቱ ኃይል ባለመኖሩ ህብረተሰብአችን ሊጠቃና ሀገሩን እንደ ህብረተሰብ ሊመሰርት አልቻለም።

እንግዲህ የኢህዴግን አነሳስ ስንገመግም ከዚህ የተበላሸ ባህልና የተወላገደ የኢኮኖሚ ዕድገት በመነሳት ብቻ ነው። የፈለገውን ያህል የማርክሲዝምን ካባ ለበስኩ ቢልም የህብረተሰብአችን መዘበራረቅና የባህል መዳከም የግዴታ ኢህአዴግ/ ወያኔ ብሄራዊ ባህርይ ሊይዝ አላስቻለውም። ከሀገር ይልቅ በክልል መንፈስ በመጠመዱና የከፋፍለህ ፖሊሲን መሳሪያ በማድረግ የሀገራችንን የህብረ-ብሄር ግንባታ ለብዙ ዐመታት ወደ ማስተላለፍ ተያያዘው። ከውጪ ኃይሎች ጋር በመመሰጣጠር ህብረተሰብአችንን ይበልጥ ማዘበራረቅና ህዝቡም አቅመ ቢስ እንዲሆን አደረገ። የእንግሊዝና የአሜሪካን የፊናንስ ኦሊጋርኪዎች ሂቲለርን ስልጣን ላይ እንዳመጡትና ጀርመን ከውስጥ እንድትፈራርስና ኃይሏም እንድትዳከም እንዳደረጉ ሁሉ ኢትዮጵያም እንደዚህ በውስጣዊ ኃይል መዳከምና መበታተን አለባት። ለዚህ ወያኔ አመቺ መሳሪያ ሲሆን ፣ ተግባሩ ደግሞ በክልል ፖሊሲ የሚገለጽና በኒዎ ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚጠናቀቅ ሆነ። ዛሬ የምናያትን ኢትዮጵያን ተጎናጸፍን ማለት ነው። ይህንን ሀቅ መሳትና ማየት አለመቻል የነገሮችን ሂደት ለመረዳት አለመቻል ብቻ ሳይሆን የዓለም ማህበረሰብና ታሪክ እንዴት እንደተዋቀረ ለመገንዘብ አለመፈለግ ነው። ከዚህ ስንነሳ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለግንቦቱ ምርጫ ሲነሱና ቅንጅትን ሲመርጡ ምኞታቸውና ፍላጎታቸው ከዚህ የተሻለ ሁኔታ ይመጣል ፣ ሀገራችንን እንደ ሀገር ለማየት እንበቃለን ፣ ከዚያም እፎይ ብለን ለመኖር እንችላለን ብለው በመገንዘብ ብቻ ነው።

## የግንቦቱ 1997 ምርጫና የብሄራዊ ነፃነት ጥያቄ

የግንቦቱ ምርጫ ከመካሄዱ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ህዝባችን ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ወጥቶ በአገዛዙ ላይ ያለውን ጥላቻ ሲያሳይና በምርጫውም ሲያረጋግጥ በእርግጥ የብሄራዊ-ነፃነትን ጥያቄ እንደ መፈክር ይዞ እንዳልወጣ ግልጽ ነው። ይሁንና በ15 ዐመታት የኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ብሄራዊ ክብሩ እንደ ተደፈረ በይፋ እንኳ ባይሆን ወስጥ ለውስጥ ሲያጉረመርምና ምን ቀን መጣ እያለ በዚህም በዚያም ሲያሰማ ከርሟል። ከላይ እንደሰፈረው ፣ በመሰረቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ነፃነት መደፈር የተጀመረው ፣

የኤርትራን ጥያቄና የክልልን ፖሊሲ ወደ ጎን ትተን ፣ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ህዝቦች መሰረታዊ ፍላጎት የሚፃረርና ህብረተሰቡን እንደ ህብረተሰብ ማስተሳሰር የማይችል ፣ እንዲያውም መንፈሱንና የመፍጠር ችሎታውን የሚያዳክም በአይ ኤም ኤፍና በዓለም ባንክ የበላይነት የረቀቀውን የኒዎ ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ሲቀበልና ተግባራዊ ሲያደርግ ነው። በታሪክ ውስጥ እንደታየው የአንድ ሀገር ብሄራዊ ነፃነት ሊከበርና ህብረ-ብሄር (Nation-State) ሊጠናከር የሚችለው በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ወይም ይህንን የሚያመቻች የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ሲሆን ብቻ ነው። በኢኮኖሚ ፖሊሲ ፣ በህብረሰተቡ መተሳሰርና መጠናከር እንዲሁም ደግሞ በባህል ዕድገት መሀከል የጠበቀ ግኑኝነት ስላለ ፣ የአንድ ሀገር ዕድገት ሊዛባም ወይም ደግሞ መልክ ሊይዝ የሚችለው አገዛዙ በሚከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካይነት ብቻ ነው። የኒዎ ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ በኢትዮጵያ ምድር ተግባራዊነት መሆን ደግሞ የውጪ ኃይሎች በውስጥ ፖሊሲያችን ገብተው እንዲፈተፍቱ መንገድ ይከፍትላቸዋል ማለት ነው። ባለፉት አስራ አምስት ዐመታት በሀገራችን ምድር የሆነው ይህ ነው።

በኢኮኖሚ ፖሊሲው ተግባራዊነት ብዙ ሰዎች ከስራ መስካቸው ሲባረሩ የህብረተሰቡ የመኖር ኃይል መናጋት ይጀምራል። ይህ በራሱ የህዝቡን ስነ-ልቦና ወደ መንካት አመራ። ሰፊ መሰረት የሌለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ሲሆን በተለይም ወጣቱ መመኪያ ማጣት ጀመረ። ይህ በራሱ የህብረተሰብ ቀውስ ሊያስከትል ቻለ። በፖሊሲው መሰረት የውጪው ንግድ ክፍት ሲሆን ከፍጆታ ዕቃዎች ጋርም የወጣቱን ጭንቅላት የማሰብ ኃይል የሚያዳክሙ ልዩ ልዩ ፊልሞችና አጸያፊ ተግባሮች በመግባታቸው በወጣቱ ትውልድና በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝቦች መሀከል አለመግባባት ይፈጠራሉ። በስራ መስክ ዕጦት ምክንያት ወጣቱ የወላጆቹ ሸክም ሲሆን ፣ መሻከሩ ይባባሳል። ይህ ጉዳይ ይበልጥ የህብረተሰቡን አቅመ ቢሰነት ያሳየበትና ይበልጥ ወጣቱንና ህፃናትንም ጭምር ለቆሻሻ ባህል ያጋለጠበት ጉዳይ ነው። ከዚህ ወልጋዳ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ መሆንና የሀገሪቱ በር ለቅ መሆን ጥንታዊ የሆኑትን የክርሰቲያኑንና የእስላሙን ሃይማኖት የሚያናጉ ሌሎች ሃይማኖቶች ሰርገው በመግባት ተጨማሪ ህብረተሰብአዊ ቅራኔዎች ፈጥረዋል። ባጭሩ ከኢኮኖሚው ፖሊሲ ተግባራዊነት መሆንና በራችን ተከፍቶ መሰጠት ጋር የህብረተሰቡ ኃይል አሰላለፍና አሰተሳሰብ ወደ ማይሆን አቅጣጫ እንዲያመራ ተገድዷል። ይህ እንዴት ከአሜሪካንና ከእንግሊዝ የውጭ ፖሊሲና የህብረተሰብ አወቃቀር ጋር ሊያያዝ ይችላል ?

እስካሁን ድረስ ለብዝዎቻችን ግልጽ ያልሆነው ነገር አሁን ባለው የግሎባላይዜሽን ግፊትና ሀገሮችን የማሰጨነቅ ዘመን እንዴት አድርገው እንደኛ ያሉ ሀገሮች ህብረሰተብአቸውን ሊያጠናክሩ ይችላሉ ፣ እንደ ነፃ ሀገርሰ የየራሳቸውን ፖሊሲ ነድፈው ለህዝቦቻቸው መከታ የሆነ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የውስጥ ገበያን የሚያዳብር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ የሚል ከባድ ጥያቄ ነው። አንዳንዶች በየዋህነትም ሆነ ሬል ፖለቲካ በሚባለው አረማመድ በመጠመድ በህብረተሰብ ዕድገትና ሀገር እንደ ሀገር ሆኖ መታየትና በሳይንስ የተፈተነ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን መሀከል ያለውን ግኑኝነት ማየት ስለማይችሉ ወይም ስለማይፈልጉ ሀገራቸው ልትወጣ የማትችለው ህብረተሰብአዊ ቀውስ ውስጥ እንድትወድቅና ህዝቦቿም አለኝታ እንዲያጡ መንገዱን ያመቻቻሉ። ይህንን በሀገራችንም ሆነ በብዙ የአፍሪቃ ሀገሮች የሰፈነውን ታሪካዊና ህብረተሰብአዊ ንቃተ ህሊና ማነስ የተገነዘቡት የምዕራቡ ዓለም ፣ በተለይም እንግሊዝና አሜሪካ በሊበራል ኢኮኖሚና በነፃ ንግድ ፖሊሲ አማካይነት በቀጥታም ሆነ በተዛዋዋሪ ወጥመድ ውስጥ በመክተት ሊወጡ የማይችሉበት ሁኔታ ወሰጥ መክተት ችለዋል። ለዚህ ደግሞ እንደ አይ ኤም ኤፍ ፣ እንደ ዓለም ባንክ ፣ የዓለም ንግድ ድርጅትና የአውሮፓ አንድነት የነፃ ንግድ ፖሊሲዎች አመቺ መሳሪያዎች ናቸው። እነዚህ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ የተቋቋሙት ኢንስቲቱሽኖች የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሳሪያዎች በመሆን ባለፉት ስድሳ ዐመታት ብዙ የሶሰተኛውን ዓለም ሀገሮች በዕዳ በመተብተብ ፣ በነፃ ንግድ አማካይነት ዕቃዎችን አግብቶ በማፍሰስና ደካማ ኢንዱስትሪዎችን በማፈራረስ ብዙ የአፍሪቃ ሀገሮችና ኢትዮጵያንም ጭምር እንደ ህብረተሰብ መኖር እንዳይችሉ ያደረጉ ናቸው። ከዚህ ጭነትና ጥገኝነት መላቀቅ የቻሉት አንዳንድ የእሲያ ሀገሮች ፣ ደቡብ ኮሪያ ፣ ሲንጋፖር ፣ ታይዋን ፣ ማሌዢያና ዛሬ ደግሞ ቻይናና ህንድ ብቻ ናቸው። ባለፉት አስራ ስምንት ዐመታት ረሺያን እንደ ህብረተሰብ እንዳትኖርና ለማፈራረስ የተደረገው ሙከራ ከስምንት ዐመት ጀምሮ በፕሬዚደንት ፑቲን ቆራጥና ወደ ውስጥ ያተኮረ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ከሽፏል። በፕሬዚደንት ዬልሲንና በአንድ ምሽት ከኮሙኒስትነት ወደ ኒዎ ለበራልነት በተለወጡት ወጣት ኢኮኖሚስቶች ተግባራዊ የሆነው የገበያ ኢኮኖሚ ፍልስፍና የራሺያንን ህብረተሰብ ሲያናጋና የተወሰነውን ህብረተሰብ ደግሞ ሲያደልብ ፣ የምራቡ ዓለም ደግሞ በዚህ በመደሰት የራሺያን የተፈጥሮ ሀብት የሚዘርፍበትና የአቶም ኃያልነቷንም የሚያዳክምበት ዕድል ያገኘ መስሎት ነበር። ይሁንና ግን ይህ የተዘበራረቀ ሁኔታ

በፕሬዚደንት ፑቲን ፈጣንና ጠንቃቃ ፖሊሲ ሲከሽፍ ፣ የምዕራቡን ዓለም ደግሞ ይበልጥ አስደንግጧል። እንደገና ከአሜሪካን ጋር መወዳደር እንደምትችልና የአቶም መሳሪያውንም እንደምታሻሽልና የሀገር አቋራጭ ሚሳይል እንደምትሰራና አሁን በቅርቡ ደግሞ ስርታ እንደሞከረች ማንነቷን ስታረጋግጥ ፣ የምዕራቡ ዓለም ራሺያን የማፈራረሱ ህልም እንደ ቅዠት ሆኖ ሲያባንነው ይታያል። ዛሬ ፕሬዚደንት ፑቲን በየሄዱበት ደረታቸውን ፊታ አድርገው ሀገራቸውን አስከብረው የሚከራከሩና የሚፈሩ መሪ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ የምዕራቡ ደራሲዎች ፕሬዚደንት ፑቲን እንዴት „የምዕራቡን ዓለም እንዲፈራ አስተማሩት“ ብለው እንዲጽፉ ተገደዋል።

ከዚህ በጣም ቀላል ግን ደግሞ የተወሳሰበ ሁኔታ ስንነሳ በተለይም አሜሪካን በተለያዩ ሀገሮች ገብቶ ህብረተሰብን እንደሚያዘበራርቅና ወደ ጦርነትም እንዲያመሩ ማድረግ ለብዙዎች ግልጽ የሆነ አይመስልም። በህብረተሰብ ፣ በህብረ-ብሄርና(Nation-State) በጠንካራ ግን ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መንግስትና በግለሰብ ነፃነት መሀከል ያለው ዲያሌክቲያዊ ግኙኝነት ግልጽ ባለመሆኑ የአንድን ህብረተሰብ መፈራረስ በግልጽ ከሚመጣ ወረራ ጋራ ነው የሚያይዙት። ለዚህ ነው በ 8.10.2007 ዓ.ም ከእኔ ለልዑካኑ የቀረበው ሀተታና ጥያቄ ግንዛቤ ውስጥ ያልገባና „ አሜሪካንና እንግሊዝ ኢትዮጵያን እንዴት ማፈራረስ ይችላሉ ? እኔ አይገባኝም ተብሎ“ የተመለሰው። ይህ በዚህ ልዑካን ብቻ ሳይሆን በሌላ ቦታም ሲነገርና አሜሪካንም የኢትየጵያን መጠንከር እንደምትሻና የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድልም ከአሜሪካን ፖሊሲ ጋር እንደተያያዘ ሆኖ የቀረበው። በህብረ-ብሄር አመሰራረት ታሪክ ውስጥም አንድ ኃያል መንግስት የሌላውን ሲሻና ለመጠናከርም ዕርዳታ ሲሰጥ ታይቶ አይታወቅም። እንግዲህ በዚህ መልክ እንዴት ተደርጎ ለአንድ ነፃ ህብረተሰብና ለተከበረች ኢትዮጵያ መታገል ይቻላል? እንዴትስ ግለሰብአዊ ነፃነትን መቀዳጀት ይቻላል ? እንዴትስ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ለውስጥ ገበያ ሰፋ ያለ መሰረት ሊጥል የሚችል የኢኮኖሚ መሰረት መጣል ይቻላል ? እንዴትሰ ህብረሰብአዊ ስምምነትንሰ ማምጣት ይቻላል። ደጋግሜ ለማሳየት እንደሞከርኩት ዛሬ ኢትዮጵያችንም ሆነ ብዙ የአፍሪቃ ሀገሮች የገቡበት ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀልና አስተዳደራዊ ጉድለት መሰረታዊ የሆነውን ሳይንሳዊ የዕድገት መመሪያና አቅጣጫ በፍጹም ለመረዳት ያለመቻል ወይም ካለመፈለግ የመነጨ ነው። ሁኔታዎች ግልጽ ሆነው ቢታዩም እንኳ ሁላችንም ቀናውን መንገድ ከመፈለግ ይልቅ ወደ ማጥ ውስጥ መግባቱን የመረጥን እንመስላለን። ተገዶ ጦርነት ውስጥ ለመሳተፍ እንደሚሄድ ግን ደግሞ በህይወት ለመመለስ ያለው ዕድል በጣም አነስተኛ ወታደር ይመስል ነፃ ያሚያወጣውን መንገድ ከመምረጥና ለዚህም በቅንነት ከመስራት ይልቅ የመጣው ይምጣ በሚል ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜ እንደ ህብረተሰብ እንዳንኖር የሚያደርገንን መንገድ የመረጥን እንመስላለን። በተለይም ዛሬ የፖለቲካ ሙቀቱ ከፍተኛ በሆነበት ወቅት መሰረታዊና ጥልቀት ባላቸው ነገሮች ላይ ከመነጋገር ይልቅ በአጠቃላይና ሃሳብን በሚያዘበራርቁ ነገሮች ላይ ብቻ በማትኮር ሰፋና ምሁራዊ ለሆነ ውይይት በሩን እየዘጋን ነው።

በዚህ ጸሁፌ ዕምነት በምዕራቡ ዓለም ከሁለት መቶ ዐመት በፊት ብሄራዊ ነፃነትን ለማስከበርና ህብረተሰብን ለመገንባት የተደረገባቸው ውይይቶችና መስዋዕትነት የተከፈለባቸው ግለሰብአዊ ምሁራዊ እንቅስቃሴዎች በዓለም ላይ የመጀመሪያውና ሳይንሳዊ ይዘትም ያላቸው ለብዙ ህብረተሰቦች የሚያገለግሉ መመሪያዎች ናቸው። ይህ ዐይነቱ ምሁራዊ ትግልና የጭንቅላት ስራ ግን እንደየ ሀገሮች ባህልና ታሪካዊ ሁኔታ መመንዘር መቻል አለበት። በአንድ በኩል ሊበራል ዲሞክራሲንና ነፃ ገበያን ተግባራዊ እናደርጋለን እየተባለ በሌላ ወገን ደግሞ ፍቱንና ህብረተሰብአዊ መረጋጋትንና ዕድገትን የሚያመጣውን ሀሳብ የምዕራቡ ዝባዝንኬ ነው እያሉ ቁጥር ውስጥ አለማስገባት አላዋቂነት ነው። ከተቃወሙ ሁለቱንም መቃወምና ብቸኛ የምንለውን ኢትዮጵያዊ የአማራጭ መንገድ ማሳየት አለብን። አሁንም በዚህ ጸሁፌ ዕምነት ልንቀበላቸውና ተግባራዊ ልናደርጋቸው የምንገደድ ዓለም አቀፋዊ ዕውቀቶች አሉ። ከዚህ ልናመልጥ አንችልም። ጥያቄው የትኛው ነው ትክክለኛውና ካለብዙ ህብረተሰብአዊ ውዝግብነት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ፍልስፍና የሚለውን የመፈለጉ ጉዳይ። ይህ እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ የግዴታ መወያየት አለብን። ከመከባበር ባሻገር መከራከር አለብን። ከፍርሃት ዓለም መላቀቅና እግዚአብሄር የሰጠንን የማሰብ ኃይልና ግለሰብአዊ ነፃነት በመጠቀም ወጣ ብለንና ደፍረን መወያየት አለብን። አንድ ህብረተሰብ ከውስጥ ዕድገትን አምጥቶ ወደ ውጭ ደግሞ ብሄራዊ ነፃነቱን ሊያስከብር የሚችለው ይህንን ግለሰብአዊ ነፃነት አምኖ ከተቀበለና በሚችለው የዕውቀት ዘርፍ ሀሳቡን ማዳበርና ማሰራጨት ሲችል ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ህብረተሰብአዊ ዕድገትና ተረጋግቶ መኖር አይቻልም። ይህንን በራስ መተማመንና ለሀገር አለኝታ መሆን የሚለውን በሳይንስ የተፈተነውን ግለሰብአዊ ፍላጎትን ፣ የፈጠራ ችሎታንና ብሄራዊ ነፃነትን

*የሚያሰከብረውን ፍቱን መንገድ የአሜሪካኑ የነፃ ገበያ ፍልስፍና ይቃወማል። ለዚህ ደግሞ ወደ አሜሪካን ህብረተሰብ ውስጥ ገብቶ በተለይም ጥቁሩ አሜሪካዊ የሚኖርበትን የተበላሸ ሁኔታና በራስ አለመተማመን መመልከት ያሰፈልጋል። እራሱን የአሜሪካንን ህብረተሰብ አደረጃጀትና የውጪ ወረራ የሚቃወሙ በአሜሪካን ምሁሮች በቲዎሪም ሆነ በኢምፔሪ የተረጋገጡ አያሌ መጽሀፎችን ማገላበጡ እጅግ ጠቃሚ ነው። ሁኔታዎችን እንድናገናዝብ ይረዳናል። ሚዛናዊ ፍርድ ልንሰጥና ለብሄራዊ ቀናተኛ ግን ደግሞ አክራሪ ያልሆነ ፖለቲካ ልንከተል የምንችለው በራሱ የአሜሪካን ምሁሮች የጻፋትን ስንመለከት ብቻ ነው።*

*የግንቦቱ ምርጫ በአዲስ መንፈስና ለአዲስ ኢትዮጵያ እንዲሁም ለብሄራዊ ነፃነት እንድንታገል በር የከፈተ ሰፊ ህዝባዊ እንቅስቃሴና ውስጣዊ ፍላጎት ነው። ህዝባችን በተለይም ባለፉት አስራ አምስት ዐመታት የደረሰበትን ማቴሪያላዊና የመንፈስ ድክመት ይብቃኝ ብሎ ሲነሳ ለመጪውም ትውልድ በጸና መስረት ላይ ልትገነባ የምትችል ኢትዮጵያን ተግባራዊ ለማድረግ በማሰቡም ነው። ይህንን ለመገንዘብ ያለመቻል ፣ በዚህም በዚያም ብሎ አውቆም ሆነ ሳያውቁ ለማክሸፍ መሞከር የታሪክ ኃላፊነትን ለመወጣት ያለመቻል ነው። አንድ ህብረተሰብ እንደ ህብረተሰብ መዳበር የሚችለው ፣ ግለሰብአዊ ነፃነት ተግባራዊ ሆኖ ብሄራዊ ነፃነት የሚከበረው ይህ ህዝባችን የሚፈልገውን ከሃምሳ ዐመት በላይ ፈጀውን ትግል ተግባራዊ ልናደርግበት የምንችልበት የቲዎሪ መሳሪያ ስናገኝ ብቻ ነው። ስለዚህም ህልማችን በጣም ቆንጆ ኢትዮጵያን ማየት እስከሆነ ድረስ ከገባንበት የቲዎሪ ውዥንብር መላቀቀ አለብን። የሰከነና ግልጽ ውይይት ማድረግ መቻል አለብን። ይህንን ካደረግን ወይንም ዝግጁ ከሆን የታሪክ ኃላፊነትን ተወጣን ማለት ነው። የነፃነቱም መንገድ ቀና ይሆናል። በመሀከላችን ያለውም መጠራጠርና አለመግባባት ይወገዳል።*

**ፈቃዱ በቀለ**


*ይህንን ጸሀፊ በሚቀጥለው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ* !!

**fekadubekele@gmx.de**